# «ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አታሸንፉ»
# ሮሜ 12፥21

## ትዕይንት ፩

*መጋረጃው ሲከፈት 3 ሰዎች ይታያሉ። እነሱም 1 እናት 1 ወንድ ልጅ 1 የእናትየው እህት(የልጁ አክስት) ተቀምጠው የግላቸውን ንግግር ሲነጋገሩ የሰማል።*

አክስት፦ ቆይ አንቺ ይህን ልጅ እስከመቼ ነው እንዲህ የምትጫወቺበት? ትምህርት አታስገቢው ምን አትይው፤ ምን ልትሆኚ ፈልገሽ ነው ለመሆኑ?

እናት፦ ታድያ እኔ ከየት አምጥቼ ትምህርት ላስገባው? ለመመዝገቢያ ብቻ 15 ብር ይላሉ። አቅሜን እያወቅሽው እንዲህ ስትይ ትገርሚያለሽ።

አክስት፦ አንቺ እኮ እኔ አውቃለሁ፤ ሁሌም እንዳሾፍሽ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ትምህርት ላይ ቢሆን ኖሮ ይሄኔ ጨርሶ ካንቺ አልፎ ለኔም ይተርፍ ነበር። ነገር ግን ምን ያደርጋል ታዲያ አንቺ እንዲህ ያለ ሰው ሆንሽ።

እናት፦ በቃ ካሁን ወዲያ እንጀራም ቢሆን ጋግሬ ልጄን ለማስተማር እሞክራለሁ። የበፊቱ ይበቃኛል። ድህነቴን እንደሆነ ማንም ያውቀዋል።

አክስት፦ ምንድነው እሞክራለሁ የምትይው። ካረጀ በኋላ ነው ትምህርት ቤት የምታስገቢው። ከዚህ ቀደምም እንደዚሁ ስትይ ነው ለዚህ ያበቃሽው። በቃ አሁን ማድረግ ያለብሽ ልጁን ለኔ መስጠት ብቻ ነው ያለሽ አማራጭ። አክስቱ ነኝ እኔም አስተምረዋለሁ። ስጭኝ ትሰጭኝ እንደሆን ልጁን።

እናት፦ እሱን ሰጥቼ እኔ ብቻዬን እንዴት ልኖር እችላለሁ?

አክስት፦ ድሮ እንደምትኖሪው ሁሉ በየሰው ቤቱ እየሰራሽ ኑሪያ። ልጁን እንደሆን እኔ ለቁም ነገር አበቃልሻለሁ።

እናት፦ በቃ። እሺ። ካልሽ ውሰጂው። የእህት ልጅ በይወልዱትም ልጅ ነው። ታዲያ አደራሽን መቼም ከኔ በላይ እንደምትንከባከቢው እተማመናለሁ።

አክስት፦ ምን ይሆናል ብለሽ ነው? ህፃን አይደል።

እናት፦ ኩኩሽ፡ ኸረ ኩኩሽ፡ አንተ ኩኩ ብላ ስትጣራ ልጁ ሮጦ ይመጣል። በል ከአክስትህ ጋር ትሄዳለህ ተዘጋጅ። እሺ ተባብለው ሲጨርሱ መጋረጃ ይዘጋል።

## ትዕይንት ፪

*መጋረጃ ሲከፈት 3 ወንድ ልጆች መድረክ ላይ ቁጭ ብለው ይታያሉ። ታላቅየው ስንታየሁ ይባላል።*

ስንታየሁ፦ አቦ ምን አይነት ጣጣ ነው አሁንስ እኔ የሚረዳኝ አጣሁ። ባንድ ጎን መኪናዋ ስትበላሽ ባንድ በኩል እዚህ ስራው ሌላ ነው። እማዬ ምን ልትሆን ነው? አትመጣም እንዴ? ስራው መብዛቱን እያወቀች ይሄን ያህል ግዜ ፈጀች። ሁለተኛው ታለቅ የዋሁ ልጅ ተሾመ ይባላል።

ተሼ፦ አንተ ስንታየሁ/3/ እነዚያ የሚታዩት ሰዎች እነ እማዬ ሳይሆኑ አይቀሩም? እስቲ እይ ብለው ሁሉም አንጋጠው ወደ ውጭ ያያሉ። ትንሽዬው ልጅ አቢ ይባላል፤ የመጨረሻው ጬጬ ልጅ ነው።

አቢ፦ እጭ ብሎ ይቆጣና። እማዬ ከቡቱቷም ልጅ ጋር ነው የምትመጣው።

ተሼ፦ ወይኔ እራሷ እማዬ ነች። ማንን ነው ይዛልን የመጣችው?

አቢ፦ ተሼ ቆይ እዚያ የአክስቴ አገር ቡቱቲያሞች ብቻ ነው እንዴ የሞሉት?

ተሼ፦ አንተ እንዴት ቡትቷም ትላለህ? ደሃ ቡትቷም ነው እንዴ የሚባለው? ባለጌ።

ስንታየሁ፦ ተነሱ እንጂ እማዬን እንቀበላት። ብለው ሮጠው ወደ እናታቸው ይሄዳሉ። አብረውም ወደ ቤት ሄደው ይቀመጣሉ። እናትዬውም ብዙ ሰላምታ ካቀረበችላቸው በኋላ መጣሁ ተጫወቱ ብላ ወደ ጓዳ ትገባለች።

ተሼ፦ ከናትየው ጋር የመጣው ልጅ ተነጥሎ ለብቻው መሬት መቀመጡን ሲያይ፦ ውይ ና እዚ ጋር ተቀመጥ ለምን ከኛ ተለይተህ እዚያ ብቻህን ተቀመጥክ?

አቢ፦ ባክህ ተወው እዚያ። የኛ ወንበር ላይ የማንም ቡቱቷም ነው እንዴ የሚቀመጠው?

ስንታየሁ፦ እውነቱን ነው ያለው እዚያው ይቀመጥ። ይላሉ እየ ተመነጫጨቁ በመናገር።

ተሼ፦ ለምን? አይሆንም። እዚጋ መቀመጥ አለበት። ና እዚህ ቁጭ በል። ብሎ ያስቀምጠዋል።

አክስት፦ ውይ እንዴት አዝነህለታል? መቀመጫው ላይ በስርአት ታስቀምጥልኝ? ወይ ጉድ። አሱም ቂጢጥ ብሎ ሲቀመጥ ትንሽ አይሰማውም። በልና ውረድ። በልኮ ውረድ። ብላ ትቆጣዋለች።

*ከመቀመጫው አውርዳ እያመናጨቀች ይዛው ስትገባ መጋረጃው ይዘጋል።*

## ትዕይንት ፫

*መጋረጃው ሲከፈት ሴትዬዋ የአንድ ሐብታም ሰውዬ በር ላይ ከልጁ ጋር ቆማ ትታያለች። ልጁ ቡቱቱ እንደ ለበሰ ነው።*

**አክስት፡-** በል እስክጠራህ ድረስ እንዳትመጣ። በል ቁጭ በል። ትለውና አስጠንቅቃው ትሄዳለች፤ ሐብታሙ ሰውዬም አምሮበት እቤቱ ቁጭ ብሎ ይታያል። ልጁም እንደ ለማኝ በር ላይ ቁጭ ብሏል። ሰውዬውም እንደ ጠበቃት፡ ሴትዬዋ አንኳኳታ ገብታ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፡- ያንን ባለፈው የጠየኩኝን አገኘሽህ ወይስ እንዴት አደረግክ?

**አቶ በላቸው፡-** ምን አገኛለሁ እሜትዬ፤ አንቺን አይደል የምጠብቀው።

**አክስት፡-** እኔን ነው እንዴ እስከ ዛሬ ስትጠብቅ የቆየኸው?

**አቶ በላቸው፡-** አዎ! ያልሽኝን ዘነጋሽው እንዴ?

**አክስት፡-** ኧረ አልዘነጋሁም። እያሰብኩበት ነበር እስከ ዛሬ። ከብዙ ውጣ ወረድ በኋላ ላገኝ ችያለሁ። ያው እዚያ በር ላይ ተቀምጧል። እንግዲህ ገንዘቡን በየቀኑ ለኔ ነው የሚሰጡኝ።

**አቶ በላቸው፡-** ጎሽ ኧረ እግዚአብሔር ይስጥሽ። እኔ ምን ቸግሮኝ እያመጣሁ ላንቺ ነው የማስረክበው። የታለ ኧረ ይግባ። ብሎ እርሱ ተነስቶ ያስገባዋል። ጎሽ ግባ ልጄ ብሎ ያስቀምጠዋል።

**አክስት፡-** በልእንግዲህ እኔ በጣም ስለምቸኩል ልሂድ። ብላ ትነሳለች። ወደ ልጁም ዘወር ብላ በል አንተ ቀጥ ለጥ ብለህ እሱ የሚያዝህን ሁሉ እንድትፈፅም። አለዚያ ግን ዋልህ። ብላ አስፈራርታና አስጠንቅቃው ትሄዳለች። *መጋረጃው ይዘጋል።*

## ትዕይንት ፬

*መጋረጃው ሲከፈት አቶ በላቸው ከኩኩሽ ጋር ይታያል።*

**አቶ በላቸው፡-** አንተ። በል። እዚያ ወደ ማሳው ወጣ እንበልና ከብቶቼን ላሳይህ። ብለው ይወጣሉ። በል አንተ ታያለህ እነዚያ ከብቶች በሙሉ የኔ ናቸው። እነዚያ ጥጆቼ ናቸው። እንዳይጠፉብህ ተጠንቅቀህ ጠብቅ። በተለይ ደግሞ እያት አየሃት እዚጋ ያቺ ቡሬ ላም ትታይሃለች? በጣም ቀልቃላ ላም ነች። የሰው እህል በልታ ኋላ አፈላማ እንዳልጠየቅ በርታልኝ። አደራ በደንብ ጠብቅ። እየው ገና ካሁኑ መንቀልቀል ጀመረች። ብሎ አስጠንቅቆት ትእዛዝ ሰጥቶት ከአጠገቡ ይሄዳል። ይሄን ሁሉ ሲናገር በጣቱ ወደ ህዝቡ እያመለከተ ነው።

**ኩኩሽ፡-** እሺ እጠብቃለሁ። ብሎ ትእዛዝ ከተቀበለ በኋላ ሰውዬው ዘወር ሲል ስራውን ጀመረ። አንቺ ሄጅ ሄጅ። እውነትም ቀልቃላ ላም ነች። ሄጅ እያለ ይጮሃል። አንዷት ዘፈን አለችው ዘፋኙ ኩኩሽ፡- ሎሚ ተራ ተራ/4/ አምዬን አደራ ይላል። ወይኔ እማዬ ለመሆኑ በጤናሽ አለሽልኝ። ወይኔ እናቴ። እያለ ከብት የሚያግድበትን ዱላ ተደግፎ ሲያዝን ከብቶቹ እሰው ማሳ ገብተው እየበሉ ነው። ወይኔ ወይኔ ምን እባላለሁ? ምን አይነት ቀልቃላ ላም ነች ብሎ ጮሆ እያለቀሰ በህዝቡ መሃል ላሚቱን ለመመለስ ሮጦ በሌላ በር ተመልሶ ይመጣል። ላሚቷን መመለሱ ነው። አሁንም በተቀመጠበት ሆኖ ሎሚ ተራተራ ሲል ከብቶቹ የሌላ ሰው ማሳ ገብተው እህል ይበላሉ። በዚህ አጋጣሚ ባለ እህሉ(ባለ ማሳው) መቶ ይጮህበታል። የአቶ አሰፋ ማሳ ነበር።

**አቶ አሰፋ፡-** አንተ… አንተ… ብሎ ካስደነገጠው በኋላ እዚህ ቁጭ ብለህ እህሉን ታስፈጃለህ? በደንብ አትጠብቅም? ከርፋፋ አፈር ድሜ ያስበላህና። የማነው ከርፋፋ። በልኮ ቁጭ ብሎ ያየኛል እንዴ ደግሞ። ተነስተህ አትመልስም? ማሳ እስኪገቡ ነው የምትጠብቀው? ድንበር አልፈዋል ምን ትጠብቃለህ እዚ?

**ኩኩሽ፡-** እሺ ብሎ ሮጦ ይመለስና ስለ ላሚቷ ክፋት ያወራል።

**አቶ አሰፋ፡-** አንተ ናስቲ። የማነህ ከርፋፋ ለመሆኑ? እህ እህ በከብቶቹ አወኩህ። የአቶ በላቸው ልጅ ነህ አይደል? ኧረ እርሱ እንደዚህ አይነት ነገር አያውቅም። አሁኑኑ ሄጄ እነግረዋለሁ። አሁን አፈር መሬት ያስበላህ የል። እነግርልሃለሁ ጠብቅ ትጠብቅ እንደሆን። ብሎ ይሄዳል ልጁም ጥበቃውን ይቀጥላል። ትንሽ ዘግየት ይልና አቶ በላቸው ባለ ከብቱ ይመጣል።

**አቶ በላቸው፡-** ኧኸኸኸ… በሎ ከሳቀ በኋላ ኧኸኸኸ…ቆይ አንተ ማጋጥ ጠብቀህ ሞተሃል። ገና አንድ ዓመት ሳትጠብቅ አፈላማ ልታስበላኝ ነው። አንተ ውርጋጥ።

እያለ ከዘራውን ከመሬት እያጋጨ፡- በል በል ከዛሬ ጀምሮ እኔ አልፈልግህም። ጓዝህን ጠቅለህ ውጣልኝ። ያቺ ሴትዮም እኔን ስታታልል ደህና ልጅ ነው ብላ አስገባችህ። በል አኮ ሂድ እኔ አሁን ሌላ አግኝቻለሁ። ብሎ ተቆጥቶ ሲጮህበትና በከዘራው ሲያስፈራራው መጋረጃው ይዘጋል።

## ትዕይንት ፭

መጋረጃ ሲከፈት ስንታየሁ፣ ተሾመ፣ አቢና እናታቸው አንድ ቦታ ተሰብስበው ተቀምጠውና ስለ ራሳቸው አንዳንድ ነገር ሲነጋገሩ ሲጫዋወቱ ይታያል።

ተሼ፦ እማዬ… ያኔ ያመጣሽው ያ ደሃ ልጅ ምስኪኑ ልጅ አመት አለፈው እኮ የት አድርሰሽው ነው የመጣሽው ያኔ። ወደ ቤት መለስሽው እንዴ?

እናት፦ በልኮ ዝም በል። ምን አገባህና ነው ይሄን የምትለፈልፈው ደግሞ። ብላ ተቆጥታ እንዳበቃች ልጁ ከች ይላል። ተጨቃጭቀው ሲያበቁ ልጁም ወደ ቤት ይገባል።

ተሼ፦ ኦ… እማዬ ልጁ ሀሜት አይችልም። ተናግሬ ከአፌ ሳልጨርስ ከች አልክ። ጎሽ እንኳን ደህና መጣህልኝ የኔ ጌታ።

እናት፦ ኧሽሽሽ… የደሃ ቀብራራ ወደ ሰማይ አራ አሉ። አንተ ምን አባህ ልትሆን መጣህ? ይሄኔ እኮ ከሰውዬው ተጣልቶ መጥቶ ይሆናል።

ተሼ፦ የትኛው ሰውዬ ነው እማ?

እናት፦ ዝም በል። ዝም በል ብዬሃለሁ ዛሬ ዋ። ወደ ልጁ ዞር ትልና(እረኛውን) ነገ ጠዋት… ነገ ጠዋት እመልስሃሁ። በል ሂደህ ውኃ ቅዳ አሁን። ሰውዬው ለራሱ የእግዚአብሔር ሰው ነው እንኳን እንተን ሌላም የማስተዳደር ሀይል አለው። ጥጋበኛ። በል ሂድና ውኃ ቅዳ። በል እኮ ሂድ። ትለውና ትልከዋለች። እሱ እያዘነና እየፈራ አንድ ነገር ልናገር ይላል።

ኩኩሻ፦ አክስቴ እህል ሳልበላ ዛሬ 3ኛ ቀኔ እኮ ነው።

አክስት፦ በል ሂድ። ውኃ ከቀዳህ በኋላ ይሰጥሀል።

ተሼ፦ ኧረ እማዬ አንድ ሰው 3 ቀን ሙሉ እህል በአፉ ሳይገባ እንዴት ብሎ ስራ ይሰራል? እኛ ብንሆን አንድ ቀን እንኳ እንውላለን እንዴ? የሱን ፈንታ እኔ ልቅዳ።

እናት፦ የምን ጠበቃ ነህ አንተ። አይሆንም። ችለህ አትቀዳም አንተ እራሱ ይቅዳ። ልጁም ውኃ ሊቀዳ እያዘነ ይሄዳል።

ሌሎቹ ተሼን፦ አስመሳይ። አዛኝ ቅቤ አንጓች። ለምን ሄደህ አትቀዳም ነበር ታዲያ። አዝነህለት ሞተህል ይሉታል በየ ተራ።

ተሼ፦ የሰው ልጅ አይደል እንዴ። ተዉ እኛም ምን እንደ ምንሆን አናውቅም እኮ። ኩኩሻም ውኃውን ቀድቶ መጥቶ እየተንገዳገደ ይወድቃል። ስለ ራበው ደክሞት። አክስት የተባለችው ግን የለችም ነበር።

ተሼ፦ እማዬ ይኸው ውኃውን ቀድቶ አመጣ። ብሎ ወደ እናቱ ይጮሃል።

እናት፦ በየት አገር ነው አንድ ጀሪካን ለያውም ይህችን የምታህል ጀሪካን ውኃ ተቀድቶ የሚበላው። በል ሂድ አሁንም ድገምና ቅዳ። ከዚያን ትበላለህ። ኩኩሻም አሁንም የባሰ ሲያዝን ሲበሳጭና ልፍስፍስ እያለ ወደ ውኃ ሲሄድ ይታያል።

ኩኩሻ፦ አሁንም አትሰጠኝ ይሆን እንዴ?

ተሼ፦ አሁንስ ከመጣ አማዬ እንደሆን አውቃ አትሰጠውም። እኔ ደብቄ እሰጠዋለሁ ብሎ እንጀራ አንስቶ ደብቆ ያስቀምጣል። ይህን ጊዜ ልጁ ይገባል ወደ ቤት። ናና አሁን እማዬ ላትሰጥህ ስለምትችል ና ላጉርስህ። ብሎ ጠቅልሎ እንጀራውን ሊያጎርሰው ሲል እናትዬው አንዳንድ እቃ በእጇ ይዛ ከኩሽና(ከጓዳ) ብቅ ስትል ድንገት አይታ ተናዳ እቃዋን ቁጭ አድርጋ።

እናት፦ እስቲ… ዋ… እስቲ… ዋ.. ዋ… እስቲ ባክህ አጉርሰው ዛሬ። አሁንም አንድ ጀሪካን ውኃ ካልጨመረ አይበላትም። አዝነህለተ ሞተሃል። ለመጨረሻ ጊዜ ሄዶ ይቅዳና እሰጠዋለሁ። ብላ ውኃውን ገልብጣ በዶ ጀሪካን ስትሰጠው አሁን ደግሞ ከወትሮው የበለጠ ተማሮ አያለቀሰ እያዘነ እየተከዘ ሲወጣ ተሼ ያየዋል። እናትዬዋ ወደ ጓዳዋ ተመለሰች።

ተሼ፦ አንተ። አንተ። አንተ ኩኩሻ… ጠብቀኝ እስቲ አሁንስ አግዝሃለሁ።

ኩኩሻ፦ አሁን እንኳን አልቀዳም እጠፋለሁ። በጣም ትንሽ ሆኜ ነበር ካገር የወጣሁት የእናቴን ሀገር ፈልጌ እገባለሁ እንጂ እንደዚህስ እስከመቼ እኖራለሁ። አሁን እኔ ልሞት ነው እረሃቡ ሊገለኝ ነው።ሲል…

ተሼ፦ አሁን በዚህ በማታ ወዴት ብለህ ትሄዳለህ? መንገድ ላይ ይጨልምብሀል። ባይሆን እንደምንም ብለህ አድረህ ነገ ጠዋት ትሄዳለህ ሲለው

ኩኩሻ፦ የፈለገ ተአምር ቢሆን እኔ ዛሬ አላድርም። እንዲህ ከምሰቃይ አውሬ ቢበላኝ ይቀለኛል። እሄዳለሁ እዚህ ከምሞት። ብሎ ሲያዝን…

ተሼ፦ በናትህ አሁን ብቻህን በዚህ በጨለማ ስትሄድ ዝም ብዬ አላይህም ጀሪካኑን እዚያ ቁጭ አድርግላትና አብረን እንሂድ እኔም ካንተ ጋር አልቀራትም ብሎ ሲያበቃ ተመካክረው ሲጠፉ መጋረጃው ይዘጋል።

## ትዕይንት ፪

መጋረጃ ሲከፈት ልጆቹ ተያይዘው ሲሄዱ ይታያል። ተሾመና ኩኩሻ ናቸው።

ተሼ፦ በቀደም እዚያ ዋሻ ውስጥ አደርን። ትላንትና ሜዳ ላይ አውሬ እንኳን ቢበላንስ እስቲ። ዛሬ በስንት ጊዜያችን የከተማ ዓይን

አየን ምነው አቦ ባልመጣሁ ኖሮ። እያለ ሲበሳጭ ሲነጫነጭ ሲማረር ይናገራል።

ኩኩሻ፦ አይዞህ ወንድሜ እኔ ለመከራ ተፈጥሬ አንተ ከኔ ጋር ስትሰቃይ የባሰ ቅስሜ ተሰበረ። እባክህ ተሸዬ አንዴ ከቤትህ ወጥተህል ለኔ ብለህ በመከራ ታገስ። ሲለው

ተሼ፦ በል እንግዲህ እዚህ ከደረስን አሁን ደግሞ ያንን ቤት አነጋግረን ለምነን እንደር።

ኩኩሻ፦ እሺ እኔ እጠይቃለሁ አንተ ብቻ በናትህ እንደዚህ አትሁን ተሳቀህ አታሳቀኝ። ተባብለው። ወደ አንድ ቤት ጎራ አሉ። አንኳኩተውም ሲጠይቁ አንድ የቤት ሰራተኛ ማነው ብላ ወደ ውጩ ብቅ አለች።

በናትሽ የሩቅ አገር እንግዶች ነን አሳድሪን። ሲላት ሰራተኛዋም በመጠየፍ አየት አድርጋ

ሰራተኛ፦ በናትሽ ይላል እንዴ ደግሞ። የት ታውቀኛለህ? እናቴንስ የት ታውቃታለህ? ብላ ከተቆጣች በኋላ፦ መጣሁ እስቲ ለሁሉም እዚህ ጠብቁኝ። ነግሬአለሁ ከዚች በር እንድ እርምጃ ብታልፉ። ብላ ከጎረቤታቸው ጋር ቡና የምትጠጣዋን ሴትዬ ታነጋግራለች።

እማዬ የሆኑ ሁለት ቡትቲያም አስጠሊታ ልጆች አሳድሩን ይላሉ በር ላይ ቆመው።

እሜቲቱ፦ በይ እስቲ ወሬሽን ተይና። ሂጂና ግቡ በያቸው። ቤት የእግዚአብሔር ነው።

ሰራተኛ፦ ግቡ ተብላችኋል። ምን አይነት ናችው ብላ አመናጭቃ አስገብታ እዚያ መሬት ተቀመጡ ትላቸዋለች። አስቀምጣቸው እሷ ለጉዳይዋ ትሄዳለች።

ተሼ፦ ብዙ ከተቀመጡ በኋላ ፈዘው አንድ ፎቶ ያያሉ። ኩኩሻም የናቱ ፎቶ መሆኑን ይናገራል። ወይኔ የማዬ ፎቶ ነው። ወይኔ እናቴ ይላል። ይሄ ሁሉ ሲሆን እሜትዬ ከጎረቤቶቿ ጋር ቡና ትጠጣለች። በድንገትም እነሱ ፎቶውን ሳያስቀምጡ ሰራተኛዋ ከች አለችባቸው።

ሰራተኛ፦ ኧ.. ኧ.. እናንተ ባለጌዎች። በሉኮ ሌቦች የሜትዬን ፎቶ ምን ልታደርጉ አነሳችሁ ወራዶች በሉ ውጡ በጤናችሁ። ብላ ተቆጥታ ታባርራቸዋለች። እነሱም ሲወጡ ሄዳ ለሜትዬ ትናገራለች። እነሱም በሌላ በር እያዘኑ ተክዘው ግራ ተጋብተው በጨለማ መሄጃ እንዳጡ ሲጓዙ ይታያል።

ሰራተኛ፦ እሜትዬ እነኚህ አሁን የገቡት ልጆች አስቀያሚዎቹ የእርስዎን ፎቶ አንስተው ሲጨማለቁ አባረርኳቸው።

እሜትዬ፦ እስቲ በዚህ በጨለማ ወዴት ይሂዱ ብለሽ ነው የምታባርሪያቸው? አፈር ያስበላሽና የእናቴ አምላክ። በይ በጤናሽ ሄደሽ ፈልገሽ ጥሪያቸው። አለዚያ አሁኑኑ ጆሮሽን ይዤ ውጪ ታድሪያታለሽ። ስትላትና ስትቆጣት በድንጋጤ ወደ ውጪ ሮጣ ትጣራለች።

ሰራተኛ፦ እናንተ ልጆች… እናንተ… ብላ ብትጣራ ማንም የለም። ሄደዋል እሜትዬ ይህን ጊዜ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ሆነው ቡና ሲጠጡ እንዲህ ይላሉ፦

እሜትዬ፦ እኔም አንድ ልጅ እህቴ ጋር አለ። ምንም እንኳን ለቁም ነገር ብላ ብትወስደውም ምን እንደሚሆን እኔ ምን አውቃለሁ። ብለው ይጨዋወታሉ ከጎረቤታቸው ጋር። ሰራተኛዋም ተመልሳ ሄዱኮ ስትላት

እሜትዬ፦ በይ ወጪ ዓይን አባሽ ይውጣና። ሁለተኛ እንደዚህ ያለ ነገር ስታደርጊ እንዳላይ። አፈር ድሜ ብይና። ብለው ሲቆጡ መጋረጃው ይዘጋል።

## ትዕይንት ፫

*መጋረጃው ሲከፈት ልጆቹ ሲንከራተቱ ይታያሉ።*

ተሼ፦ ትላንት በረንዳ አደርን። መቼም ከዚያ ከበቀደሙ አዳር ቢሻልም። ዛሬ ደግሞ እንደ ልማዳችን የለመነውን እንበላለን። ነገር ግን ቤት ገብቶ መተኛት ነው የናፈቀኝ። ይላል።

ኩኩሻ፦ አይዞህ ዛሬ ደግሞ ከበቀደሙ የተለየ ሰፈር ነው የመጣነው መሰለኝ። ለሁሉም አንኳኩቼ ከጠየቅኩ በኋላ ያሳድሩን ይሆናል ማን ያውቃል የጌታን ስራ። ብለው አንኳኩተው ሲጣሩ የበቀደሟ ሰራተኛ መጣች

ሰራተኛ፦ በቀደም እኮ ጥሪያቸው ተብዬ ወጥቼ ስጠራችሁ ጠፋችሁብኝ ቆይ አሁንም እሜትዬን ጠይቄ ልመጣ ብላ ሄዳ ተጣርታ ተናግራ እስክትመጣ ውጪ ይሆናሉ። እሜትዬ የበቀደሞቹ ሁለቱ ልጆች ዛሬም መጡ አሳድሩን እያሉ ነው።

እሜትዬ፦ ግቡ ቤት የእግዚአብሔር ነው በያቸውና ገብተው ይቀመጡ መጣሁ። ደግሞ እንደ በቀደሙ ብታመናጭቂያቸው ወየሁልሽ። ነግርኩሽ ።አልቆይም መጣሁ። ብላ ወደ ውጪ ወጣ ትላለች።

ሰራተኛ፦ ግቡ ብላ አስገብታ ወንበር ላይ አስቀምጣ እሜትዬ እስኪመጡ ቁጭ ብላችሁ ተጫወቱ። ብላ ከበቀደሙ በተለየ ሁኔታ ትቀርባቸዋለች።

ኩኩሻ፦ ወይኔ ይሄ ፎቶ ፈፅሞ የማዬ ፎቶ ነው። ወይኔ እማዬ። እያለ አንስቶ ፎቶውን እያገላበጠ ሲስም

ተሼ፦ በቀደም እዚሁ ቤት መጥተን እነደዚያ ተባረርን። ዛሬም እንድንባረር ነው እንዴ? አቦ ቁጭ አርግ። ምን እየሆንክ ነው? ሲባባሉ ሲጨቃጨቁ እሜቲቷ ከች አሉ።

እሜትዬ፦ እናንተ… ደህና ናችሁ? ብለው ሰላምታ ሰጥተው ሲገቡ እረጋ ብለው ፎቶ እያዩ የእናቱን ፊት ሲያይ እሜትዬም፦ ምንድነው ልጆች ብለው እረጋ ብለው ሲጠይቁ በተለይ ኩኩሻ፦ ወይኔ እማዬ ምን እዚህ አገር አመጣሽ ብሎ ሲያለቅስና ሲጠመጠምባት

እሜትዬ፦ የማናት እማዬ ብላ ደንግጣ  ቆማ ልጄ እንደሆን የሂኔ ኮሌጅ ሳይገባ አይቀርም። የማነህ አንተ? ብላ ጠየቀችው።

ኩኩሻ፦ እማዬ እኔ ኩኩሻ እኮነኝ። ብሎ ያለቅሳል። ዘሎም ይጠመጠምባቸዋል።

እሜትዬ፦ ወይኔ አፈር በበላሁ። ወይኔ ለጄ። እኔ አልፎልኝ እነዲህ ስንቀባረር። አንተን እህቴ ይሂኔ አስተምራ ደህና ደረጃ ታደርስልኛለች ብዬ የመንገዱን እርቀት ተመልክቼ ሳልፈልግህ አንተ ግን ምን ሆነህ ለዚህ እንደበቃህ አላውቅም ወይኔ ልጄ ብለው ያዝናሉ። ያለቅሳሉ። ይሂስ ማነው ደግሞ ይዘህ የመጣኸው?

ኩኩሻ፦ እረሳሽው እንዴ እማ? የህትሽ ልጅ ተሼ እኮነው። ያክስቴ ልጅ እኮ ነው።

ተሾመ፦ ወይኔ እኔ ትንሽ ልጅ ነበርኩ አክስቴ ስትመጣ እኛጋ። ብሎ ተነጋግረው አክስትዬውም የእንጀራ ጉዳይ እዚህ አምጥቷት ሀብታም እንደ ሆነች ትናገራለች።

እሜትዬ፦ እያለቀሱ እያዘኑ ወይኔ ልጄን። እንደዚህ ያለ እህትስ አይገኝ። አስተምርሀለሁ ለቁም ነገር አበቃሀለው ብላ ልጄን ወስዳ እንደዚህ አድርጋ በስንት አመቱ ያውም እንዲህ አድርጋ አባራ አጎሳቁላ ወይኔ ጌታ ብቻ ይይላት። ብላ ስታለቅስ ስትነጫነጭ መጋረጃው ይዘጋል።

## ትዕይንት ፰

መጋረጃው ሲከፈት እሜትዬ ተሾመና ኩኩሻ ሁነው ሲጫወቱ ቁም ነገር ሲነጋገሩ ይሰማል ይታያል።

እሜትዬ፦ በል እንግዲህ ልጄ ተሾመ፦ እናትህ ወይም እህቴ ብትበድለኝም ልጄን ብትበድለውም አንተን ግን አንበድልህም። ይኸው ከወር በላይ ከእኛ ጋር ስትዝናና እንደ ልብህ ስትሆን ቆይተሀል ከልጄጋር። አሁን ግን እናትህ በድንገት ከቤት በመውጣትህ ሳትደናገጥ አትቀርም። እናት ናትና። አሁን ልብስህንም ቀያይረሀል የትራንስፖርት ብር ልስጥህና ግባ። ለኔም ሰላም መሆኔን ንገርልኝ። ልጄም ከአንተ ጋር በሰላም አብራችሁ እዚህ መድረሳችሁን ንገርልኝ።

ተሼ፦ አዎ አክስቴ፦ እኔ ምን በድዬው ነው ብለሽ ትይኛለሽ ብዬ ፈርቼ ነው እንጂ አትለቁኝም ብዬ ፈርቼ ነው እንጂ ለነገሩማ እነሱም ናፍቀውኛል። ለሁሉም እቃው ተዘጋጀልኝ? በጊዜ ወጣ ብዬ መኪና ልጠብቅ።

እሜትዬ፦ አዎ ተዘጋጅቶልሀል። በሉ ተነሱ እንሂድ ወደ መናህሪያ ተባብለው ሲወጡ መጋረጃው ይዘጋል።

## ትዕይንት ፱

ወጋረጃው ሲከፈት የልጆቹ እናት ከ2ቱ ልጆቿ ጋር ሆነው ስትጫወት ስለ ተሾመም አንስተው ሲያዝኑ ይታያል ይሰማል። ልጁ በጣም ዘንጦ ለብሶ አምሮበት ሻንጣ ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሲያመራ ይታያል። እቤትም እንደ ደረሰ አንኳኩቶ ሲገባ ሁሉም ጮኸው ተጠምጥመውበት አልቅሰው ይቀበሉታል።

እናት፦ ወይኔ ልጄ አንተ በየዋህነትህ ሳትሞት አትቀርም። የት ነው የጠፋኸው? ልጁስ የት አለ? ለመሆኑ ከየት ነው እንዲህ ለብሰህ አምሮብህ የመጣኸው?

ተሾመ፦ እማዬ ኩኩሻ እናቱ  ጋር ገብቶ። አክስቴ እራሷ እኔን አልብሳ አሳምራ እርድ አርዳልኝ። ተጋብዘን አንድ ወር ሙሉ ከእኛ ጋር መከራዋን ስታይ ቆይታ ይኸው አሁን ደግሞ ልብስ ገዝታ እንዲ ከራሷ ወጪ አውጥታ የትራንስፖርት ሰጥታኝ ሸኘችኝ።

እናት፦ ወይኔ እኔ ልጇን እንደዚያ በድዬ አባርሬው እሷ ግን አንተን ልጄን አሳምራ ስትሸኝ። በእውነት የሚደንቅ ትህትናና ትእግስት ነው። መቼም እንደ በደልኳት ታውቃለች። ነገ ዛሬ አልልም እናንተንም ይዤ ሂጄ እግሯ ላይ ወድቀን ይቅር ትለን ዘንድ እንለምናታለን። አንተ ግን እንኳን ደህና ገባህልኝ ብለው ሲጨዋወቱ መጋረጃው ይዘጋል።

## ትዕይንት ፲

መጋረጃው ሲከፈት እሜትዬ ኩኩሻ እና ጎረቤቶቻቸው ሆነው ቡና ሲጠጡና የግል ወሬያቸውን ሲያወሩ ይሰማል። ይታያል። ተሾመ፣ እናትዬው፣ ስንታየሁና አቢ ደግሞ ሻንጣቸውን ተሸክመው ወደ ልጆቹ አክስት(ወደ እሜትዬ) ሲሄዱ ያታያል።

ብዙ ከሄዱ በኋላ በተሾመ ጥቆማ ቤቱን አገኙት። ካንኳኩም በኋላ ሰላምታ ሰጥተው ይገባሉ። ጩኸቱ በረከተ ትልልቆቹ ሴቶች(እህትማማቾቹ) ይቅርታ ተጠያየቁ። ልጆቹ ኩኩሻን ይቅር በለን አሉ። እልል ከተባለ በኋላ እንዲ ቀመጡ ተጠየቁ ታላቅ ግብዣ ተደረገ። ጎረቤት ተጠርቶ አብረው ተደሰቱ። በዚህም

አጋጣሚ መምህሬ ዮሐንስ መጡ። ሁኔታው ከተነገራቸው በኋላ እሳቸውም በነገሩ ተገርመው ባጋጣሚ መምጣታቸውን ተናግረው ሲያበቁ። ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አታሸንፉ የሚለውን የወንጌልን ቃል መሰከሩ አስተማሩ። እግዚአብሔር ይመስገን የሚለውን መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ድራማው ያበቃል።

**ተፈፀመ**